# አንቱ ተራገሙ፤ አንቱው ተደርገሙ

# የፕረፌሰር መስፍን የቅሌት ተራራ

ከቬጋስ ታዛቢ

ግንቦት 7 በተባለው ጣጠኛ የሻዕቢያ ቅጥረኛ ቡድን ጋባዥነት ይመስላል ዶክተር መስፍን ወልደማርያም (እንደ አሳቸው ገና አልባለግንምና አንቱ ልበላቸው ) ወደ ላስ ቬጋስ መጥተው መጽሐፍ ያሉትን ቡትቶ ሊያቀርቡ በጣሩበት ስብሰባ ተገኝቼ ጉድ ብዬ ጉድ ታዝቤ ወጥቻልሁ ። ለካስ ሰውየው ባለጌና ተራ ዕብሪተኛ ናቸው ? መሀይም አሉን፤ሰደቡን፤ ኢሕአፓ ተኗል ብለው በደርግ ገራፊና የሀገራቸውን ታሪክ ማወቅ በተሳናቸው ወጣቶችም ተጨበቸበላቸው ።

አክተር መስፍን የተጠየቁት ጥያቄ ተገቢ ነበር ፡፤ በ 60 ዎቹ በአማካሩት ደርግ መገደል ጉዳይ ሲነሳ ኮውንቲ ጨበጡ ። ስለ አፄ ኃይለስላሴም ያሰፈሩት በጥያቄ ገባ;፡ ደነፉ። በሰባአዊ መብት ጥያቄ ስምሪታቸው ጐዶሎና ክልልተኛ እንደ ነበር ተነገራቸው ። ኢህአፓን ሰደቡ ። ብዙ ያውም አልተጠየቁም ። ጸረ ሴት ሆነው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የዩኒቨርስቲ ሴቶችን ሊጥሉና ሊያጣሉሲሞክሩ የንበሩት አልተነሳም ። የወያኒን አፈና ተቋም አለቃ ሲሞት ሀገራችን ዛሬ ሰው አጣች ብለው የቀባጠሩትም አልተነገርም ፡፤ አማራ ሕዝብ የለም ብለው ሚሊዮን የሰደቡትንም በተመለከተ ጥያቄ አልቀረበላቸውም ። በመጠኑ አንድ ሁለት ጥያቄ ሲቀርብ አቅራቢዎቹን መሳደብ መረጡ ያ ገበናቸውን ጠንቅቆ የሚያውቀውን፤ፈሪነታቸው ሲታዘብ ይቆየውን ኢህአፓን መወረፉን መረጡ ። የሚያስገርም አልነበረም ። ፕሮፌሰር መስፍን የአሜሪካ ተገዢ ናቸውና፤ ነበሩና ። ያን ትውልድ በሶሻሊስትነት በተራማጅነትና በግራ ክንፍነት የሚከሱት ዶክተር መስፍን ሆኑም ሌሎች አድሃሪ መስሎቻችው በመሰረቱ የኋላ ቀር ስርዓትና አስተሳሰብ ባሪያዎች አለያም የባዕድ ርዕዮት የሆነው የካፒታሊዝም ደፋቂዎች ናቸው ፡፡ ግራ ክንፍና ሕዝባዊ መሆን የሚያሳፍር ሳይሆን የሚያኮራ ነው ። የድንቁርና ስርዓት ደጋፊና አቃፊ መሆን የሚያስኮንን ነው ። ዶክተር መፍን የአዋቂ አዋቂ ነኝ ለሚሉትና መሰሎቻቸውም ግብዝነታችሁን እንጂ ብልህነታቸውን አታሳዩአም የሚል ነው የሚሰጣቸው መልስ፡ የኢትዮጵያን ታሪክ የከሸፈ ብለው ካንቋሸሹ በሁላ በዚህ የጻፉትን ከልሰው አዳፍኔ ብለው ትውልድን በጅምላ አውግዘው አርበኞችንም ባንዳ ብለው የሀገርና የሕዝብ ታሪክን አጉድፈዋልና ይህ ነው የሚባል ቃፒና አስተማሪ ጽሁፍ አቅርበው የማያውቁ የደርግ የወያኔ አሽከር ሆነው የቆዩ ናቸው ። ቢከበሩ ጊዘ በሰው ራስ ላይ ቂጥ ሊሉ ከጅለውና ተጀቡነው ትውልድን ጀጋንን መስደብን የተያያዙ አንዴ በኢትዮጵያ ታሪክ ገንቢ ሚና ያልተጫወቱ ናቸው ። ለሶስት አገዛዝ ጠባይ አሳምረው ያደሩት አለምክንያት አይደለም ። ቀስተ ዳመና ሲሉም

ህብረትን ቀጥሎም ቅንጅትን ለማፍረስ መሆኑን ዜጎች ሁሉ ታዝበዋል ። ይህን ጸያፍ ገጽታቸውን በላስ ቬጋስ ይሳዩን ።

ማፈሪያ አዛውንት! እንጨትም ድንጋይም ይሸብታል ሲባል ለካ እውነት ኖሯል !

አንቱው ተሳደቡ ተርጋእሙ ፤አንቱው ግን ተዋረዱ ተደርገሙ እላቸዋለሁ ።